*አድዋ፤*

*የድል ነጋሪት ጎሳሚ*

*የኢትዮጵያውያንን ገድል ነጋሪ*

*የታሪክ ጎማ ቀያሪ*

*አድዋ ህያው፤ ለዘላለም ዓለም ኗሪ* !

## 125ኛውን የአድዋ ድል ምክንያት በማድረግ የተሰጠ መግለጫ

ዘንድሮ 125ኛ አመቱ የሚከበረው የአድዋ ድል፤ የኢትዮጵያን ነጻነትና ቀጣይነት ያረጋገጠ ብቻ ሳይሆን፤ ለሌሎች በቅኝ ግዛት ስር ለነበሩ ህዝቦች የነጻነት ትግል መባቻ በመሆንም የሚዘከር ነው። ያ ዘመን አውሮፓውያን ሀያል የነበሩበትና ዘረኛ አገዛዛቸውን በዓለም ዙሪያ፤ በተለይም በዓፍሪካ ሁሉም አገራት ላይ፤ በህይል ያሰፈኑበት ወቅት የነበር መሆኑ የሚታወቅ ነው። አውሮፓውያን የሰለጠኑ፤ የበላይ የሆኑና በማንም ሀይል ሊሸነፉ የማችሉ መሆናቸውን የሚገልጹ አስተምህሮቶችም የተስፋፉበት፤ ህዝቦችን በገዥና ተገዥ የሚከፋፍለው የቅኝ አገዛዝ ስራት *አስፈላጊነትም`* የተሰበከበት ልዩ ግዜ እንደነበር የሚታወስ ነው።

ከ125 አመት በፊት በ1888 ዓም፤ ኢትዮጵያውያን አድዋ ላይ በጣሊያን የቅኝ ገዥ ወራሪ ሰራዊት ላይ ያስመዘገቡት ድል ግን፤ በሁሉም ቅኝ ገዥ ሀይሎች ላይ የተመዘገበና ታሪክን የቀየረ ልዩ ክስተት ሆነ። በዘመናዊ መሳሪያ የታጠቀ የነጭ ሀይል፤ ለነጻነትና ክብራቸው በሚታገሉ ጥቁር ህዝቦችም ሊመከትና ሊደመሰስም እንደሚችል በገሀድ ታየ። በአገዛዝ ስር ለነበሩ ህዝቦች ሁሉ የነጻነት ጮራ ፈነጠቀ። የገገዥና ተገዥ፤ የነጭና፤ጥቁር ልዩነት ኑባሬነትን የሚሰብኩ ሀሳዊ መሲህ አስተምህሮቶች ከሸፉ። አዲስ የነጻነትና ዕኩልነት ዘመን አይቅሬነትም ተበሰረ። በዚህም ምክንያት የአድዋ ድል፤ የኢትዮጵያውያን ኩራትና ቅርስ ብቻ ሆኖ ሳይሆን፤ በቅኝ ገዥዎች መዳፍ ስር ለነበሩ ጥቁር ህዝቦች ሁሉ፤ የነጻነት መባቻ ቀን በመሆን ይታወሳል ይከበራልም።

ይህ የመላው ጥቁር ህዝቦች ጭምር አንጸባራቂ ድል የሆነው የአድዋ ስኬት እንዴትነት፤ እስካሁንም ጥያቄ የሚሆንባቸው ወገኖች አሉ።። ዳግማዊ አጼ ሚኒልክና ንግስቲቱ እቴጌ ጣይቱ ጦርነቱን በመምራት የነበራቸው የላቀ ሚና የታወቀ ነው። የኢትዮጵያውያን ጀግንነትና ያርበኝነት ታሪክ፤ ለነጻነታቸውና ክብራቸው ያላቸው ቀናኢነት፤ ለድሉ ስኬት ወሳኘነት

የነበራቸው መሆኑም ግልጽ ነው።። ከዚህ ሁሉ በላይ ግን፤ የአድዋ ድል ሚስጥር ፤ የኢትዮጵያውያን በአገራቸው ላይ ጠላት ሲነሳ፤ ባንድ ልብ፤ በአንድ ዓላማ ቆመው፤ በጋራ ለመሰለፍ ያላቸው ፈቃደኝነትና ቁርጠኝነት እንደሆነ ነው የሚታመነው። ለአድዋ ተጠርቶ የቀረ፤ አኩርፎ የሸፈተ፤ ተደልሎ የከዳ አልነበረም። ሁሉም ዓመሉን በጉያው፤ ስንቁን በትከሻው ይዞ ነበር፤ አገሩን በማስቀደም ጥሪውን ሳያቅማማ ተቀብሎ የዘመተውና በጀግንነት የተዋደቀው። ለዚህም ነው የአድዋ ድል የሁሉም የኢትዮጵያ ህዝቦች የአንድነት ትግል ውጤት የሚሆነው።

የአድዋ ድል ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን፤ በዓለም ታሪክ ከፍተኛ ክብርና ሞገስ አስገኝቷል። ኢትዮጳያ በዓለማቀፍ መድረኮች ተገቢ ቦታዋን እንድታገኝ አድርጓል። የአድዋ ጀግኖች ኢትዮጵያውያንም፤ የአገራቸው የዕድገት ደረጃና ስልጣኔ፤ ባገኘችው ድልና በተሰጣት ክብር ልክ አለመሆኑን በመረዳት፤ ለለውጥና ዘመናዊ ትምህርት እንዲተጉ ረድቷል። ይሁን እንጂ ይህ የለውጥና እድገት ጉዞ፤ ከአራት አስርት እመታት በኋላ፤ ዳግም በተከፈተባት የጣሊያን ወረራ ምክንያት የተሰናከለ ሲሆን፤ ከዚያ ወዲህም፤ ለለውጥና እድገት የተደረጉ ጥረቶችና የተገኙ ውጤቶች፤ ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን የሚመጥኑ አልሆኑም። ይልቁንም በተለይ ባለፉት ሶስት አስርት አመታት በኢትዮጵያ የተስፋፋት የልዩነትና የጥላቻ ትርክቶች፤ የተሳሳቱ የታሪክ ኑባቤዎች፤ የአድዋን ድል ውርስ የሚንዱና የአገሪቱን ቀጣይነትም ጥያቄ ውስጥ የሚያስገቡ ሁነዋል፡፤

በመሆኑም ዛሬ በ125ኛው አመት የአድዋ ድል ቀን ላይ የምንገኝ ትውልዶች፤ የአድዋ ጀግኖች፤ በዓለም ታሪክ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠውን ይህን ድል ያስገኙት፤ አንድ ላይ ሆነው፤ በኢትዮጵያዊነት ታድመውና ተሰልፈው መሆኑን በውል መረዳት ይኖርብናል። በደምና አጥንታቸው ተከላከለው ያቆዩአትን ኢትዮጵያን ቀጣይነት ማረጋገጥና፤ የዕድገት ደረጃዋንም ከሚገባት ደረጃ ማድረስ የትውልዱ ሃላፊነትና አደራም መሆኑን ተረድተን ማስረዳትና መትጋት ይጠበቅብናል። **ይህ ሲሆን ነው አድዋ ዛሬም ህያው የሚሆነው።**

ክብር ምስጋና ለአድዋ ጀግኖች!

የካቲቲ 17፤2013

በአውሮፓ የኢትዮጵያዊያን መድረክ (ድልድይ) **Address**: Borgval 2/28, 1000 Brussels, Belgium **Email:** info@dildiy.org